# ምዕራፍ አራት

# ማኅበራዊ አካባቢያችን

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ውጤቶች**

➢ ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ዓለም አቀፋዊ እውቅና ያላቸውን የኢትዮጵያን ቅርሶች ስም በመጥቀስ ጠቀሜታቸውን ትገልጻላችሁ፡፡
- የባሕል ምንነትን ለማስረዳት የባሕል ገጽታዎችን ትለያላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያ ቋንቋ ቤተሰቦችን ስም በመጥቀስ ለእያንዳንዱ ምሳሌ ትሰጣላችሁ፡፡
- በኢትዮጵያ የሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት የሚያስከትሉትን ጉዳትና የሚገቱበትን ዘዴዎች ትገልጻላችሁ፡፡
- በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አስተዋጽኦ ያበረከቱ ኢትዮጵያውያንን ስም በመጥቀስ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ትገልጻላችሁ፤ እነርሱን በአርአያነት ለመከተል ትወስናላችሁ፡፡
- በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ግንኙነቶች በመለየት ማኅበራዊ ግንኙነትን ለማዳበርና ለመግባባት የሚረዱ ዕሴቶችን በተግባር ትገልጻላችሁ፡፡
- ከዕለት ሕይወታችሁ በመነሣት መልካም አስተዳዳር ምን እንደሆነ ትገልጻላችሁ፡፡

**በምዕራፉ የተካተቱ ይዘቶች፡-**


4.1 የኢትዮጵያ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች

4.1.1 ዓለም አቀፋዊ እውቅና ያላቸው የኢትዮጵያ ቅርሶች

4.1.2 በኢትዮጵያ ያሉ የቋንቋ ቤተሰቦች

4.1.3 በኢትዮጵያ የሚገኙ ጐጂና ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶች

4.1.4 በኢትዮጵያ በተለያዩ የሥራ መስኮች ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦች

## መግቢያ

ተማሪዎች! በሦስተኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ስለ አዲስ አበባ ከተማ ማኅበራዊ አካባቢ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የቅርስን ምንነት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና በማግኘት በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ድርጅት የተመዘገቡትን የኢትዮጵያ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን በዝርዝር ትማራላችሁ፡፡ ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ የብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር ናት፡፡

## 4.1 የኢትዮጵያ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች

**ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

- ከዚህ ንዑስ ምዕራፍ በኋላ፡-
    - ዓለም አቀፋዊ እውቅና ያላቸውን የኢትዮጵያ ቅርሶችን ስም ትዘረዝራላችሁ፡፡
    - የታሪካዊ ቅርሶችን ጠቀሜታ ታስረዳላችሁ፡፡
    - ባህል አጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤ መሆኑን ትገልጻላችሁ፡፡
    - የባህል መገለጫዎችን ትጠቅሳላችሁ፡፡
    - የኢትዮጵያ ቋንቋ ቤተሰቦችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
    - ለእያንዳንዱ የቋንቋ ቤተሰብ ምሳሌዎችን ትሰጣላችሁ፡፡
    - በኢትዮጵያ የሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ትለያላችሁ፡፡
    - ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያመጡትን ጉዳቶችና መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ታስረዳላችሁ፡፡
    - ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶችን ትለያላችሁ፡፡
    - በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ስኬታማ ውጤት ያስመዘገቡ ታዋቂ ኢትዮጵያውያንን ትዘረዝራላችሁ፡፡
    - በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አስተዋጽኦ ያበረከቱ ታዋቂ ኢትዮጵያውያንን ትገልጻላችሁ፡፡
    - የታዋቂ ኢትዮጵያውያንን አርአያነት ለመከተል ያላችሁን ውሳኔ ትገልጻላችሁ፡፡

### የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

1. ዓለም አቀፍ እውቅናን ያገኙ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች
2. የታሪካዊ ቅርሶች ጠቀሜታ
3. ባህላዊ ቅርስ
4. የቋንቋዎች ቤተሰብ
5. ልማዳዊ ድርጊቶች
6. ታዋቂ ኢትዮጵያውያን

**ተግባር 4.1.1** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** ስለ ቅርስ ምንነትና ጠቀሜታ መግለጽ

**መመሪያ-** ከ4-6 በሚደርሱ ተማሪዎች ቡድን በመመሥረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ቅርስ ምንድን ነው?
- የተፈጥሯዊና የታሪካዊ ቅርሶችን ልዩነት ግለጹ፡፡
- የኦሞቲክ ቋንቋ በአብዛኛው የሚነገረው የት አካባቢ ነው?
- ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዴት ማጥፋት ይቻላል?

ኢትዮጵያ የጥንታዊ ታሪክና የተለያየ ባህሎች ባለቤት ናት፡፡ በተጨማሪም የበርካታ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ባለቤት ናት፡፡ ቅርስ የጥንት ሰዎች ወይንም ያለፈው ትውልድ የእውቀትና የሥልጣኔ ደረጃ መገለጫ ቁስ ወይንም በተፈጥሮ የተገኘ አእምሮንና መንፈስን የሚያድስ ውድ ሀብት ነው፡፡ ቅርስ ጥንታዊ ሥልጣኔን መማሪያና የሀገር ኩራት ነው፡፡

ቅርስ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ቅርስ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ በተጨማሪም ቅርስ የሚታይና የሚዳደስስ ወይም የማይታይና ረቂቅ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚታይና የሚዳሰስ ቅርስ ቁሳዊ ቅርስ በመባል ሲታወቅ የማይታይና ረቂቅ ቅርስ ደግሞ መንፈሳዊ ቅርስ ይባላል፡፡

### ሀ.ቁሳዊ ቅርስ

ቁሳዊ ቅርስ አንድ ቅርስ ቅርጹን፣ መጠኑን፣ ዓይነቱን (መልኩን)፣ ከምን እንደተሠራና ለምን ጉዳይ እንደተሠራ ለማጥናት ያስችላል፡፡ ቁሳዊ ቅርስ ሐውልቶችን፣ የሕንጻ ፍርስራሾችን፣ ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጹሑፎችን፣ ትክል ድንጋዮችን፣ በቁፋሮ የተገኙ ሳንቲሞችን፣ ጌጣጌጦችንና ዋሻዎችን ያካትታል፡፡







ሥዕል 4.1 ቁሳዊ ቅርሶች

### ለ.መንፈሳዊ ቅርስ

መንፈሳዊ ቅርስ በዓይን የማይታይና የማይጨበጥ ነገር ግን በድምፅ ወይንም በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚገለጽና አንድ ሕዝብ በቅብብሎሽ (በትውፊት) ያገኘው ሀብት ነው፡፡ ትውፊታዊ አባባሎች ወይንም ሥነቃሎች፣ ጭፈራዎች፣ ቀረርቶዎችና ሽለላዎች፣ እንጉርጉሮዎች፣ የበዓል አከባበር ክንዋኔዎችና ሌሎችም የአንድ ሕዝብ መንፈሳዊ ቅርሶች ናቸው፡፡ በብዙ የሀገራችን ክፍሎች የሚታወቀው የመስቀል በዓል አከባበር፣ የሬቻ በዓል አከባበር፣ የፍቼ በዓል አከባበር፣ የቡሔ ጭፈራና የመሳሰሉት የሀገራችን ሕዝቦች መንፈሳዊ ቅርሶች ናቸው፡፡



የጥምቀት በዓል አከባበር



የእስልምና በዓል አከባበር



የሬቻ በዓል አከባበር




የፕሮቴስታንት የጸሎት ሥነሥርዓት

*ሥዕል 4.2 መንፈሳዊ ቅርሶች*

ቁሳዊ ቅርሶች ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች መጠናቸው አነስተኛ በመሆኑና ለአያያዝ ምቹ በመሆናቸው ከቦታ ቦታ ማንቀሣቀስ ይቻላል፡፡ **ለምሳሌ፡-** ጥንታዊ የመገልገያ መሣሪያዎች፣ ሳንቲሞች፣ የብራና ጽሑፎች፣ አልባሳትና የመሳሰሉት ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ናቸው፡፡

**የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች**

የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ከአካላቸው ግዝፈት ወይንም ከመሬት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ከቦታ ቦታ በቀላሉ ሊንቀሳቀሱ አይችሉም፡፡ **ለምሳሌ፡-** የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን፣ የጎንደር አብያተ መንግሥታት፣ የሶፍዑመር ዋሻ፣ የስሜን ተራራ የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ናቸው፡፡



የጎንደር አብያተ መንግሥታት



የሶፍ ዑመር ዋሻ

ሥዕል 4.3 የማይንቀሳቀሱ ቅርሶች


ማንኛውም ረዥም ዕድሜ ያስቆጠረ ነገር ሁሉ በቅርስነት አይቆጠርም፡፡ አንድ ቁስ ወይንም ክዋኔ በቅርስነት ለመመዝገብ ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

1. ከፍተኛ የፈጠራ ሥራ የታየበት፤
2. በሥነ ሕንጻው፣ በአሠራሩና በንድፉ ዘመናትን የተሻገሩ ዕሴቶችን ማንጸባረቅ፤
3. የተረሳ ወይንም የጠፉ ባህላዊ ትውፊትን ወይንም ሥልጣኔን ማሳየት፤
4. ልዩ ተፈጥሮአዊ ውበትና ሥነ ውበታዊ ጠቀሜታ መያዝ፤
5. መልክአ ምድራዊ ለውጦችን ማሳየት፤
6. ሥነ ሕይወታዊ ለውጦችን የሚያሳይ፣ ብዝኃ ሕይወትን የሚገልጽ፣ በተፈጥሮ አካባቢ ለመጥፋት የተቃረቡ ዝርያዎች የሚገኙበት መሆን ይኖርበታል፡፡

ከቅርሶቻችን መካከል የአክሱም ሐውልቶች፣ የስሜን ተራራ ብሔራዊ ፓርክ፣ የጎንደር አብያተ መንግሥታት፣ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን፣ የጥያ ትክል ድንጋዮች፣ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ፣ የታችኛው የአዋሽ ሸለቆ፣ የሐረር ግንብና የኮንሶ እርከንና መልክዓ ምድር በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

### ሀ. የአክሱም ሐውልት

አክሱማውያን ያለዘመናዊ መሣሪያ ያቆሟቸው ግዙፍ ሐውልቶችና በሐውልቶቹ ላይ የሚታዩ ንድፎች እጅግ አስደናቂ ናቸው፡፡ የአክሱም ሐውልት የጥንት ኢትዮጵያውያንን የኪነ ጥበብ ችሎታ የሚያሳይና ከፍተኛ የፈጠራ ሥራ የታየበት በመሆኑ በዓለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግቧል፡፡





ሥዕል 4.4 የአክሱም ሐውልቶች

### ለ.የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን

የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን እጅግ ማራኪና አስደናቂ አሠራር አሏቸው፡፡ ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍለው የታነፁ ከመሆናቸውም በላይ የቀደምት ኢትዮጵያውያን ከፍተኛና አስደናቂ የሕንጻ ጥበብ ያረፈባቸው ቅርሶች በመሆናቸው በዓለም ቅርስነት ተመዝግበዋል፡፡

የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን እጅግ ማራኪና አስደናቂ ቅርጽና አሠራር አላቸው፡፡



ሥዕል 4.5 የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን በከፊል

## ሐ. የስሜን ተራራ ብሔራዊ ፓርክ

የስሜን ተራራ ብሔራዊ ፖርክ በኢትዮድያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳትና አእዋፋት የሚኖሩበት ተፈጥሮአዊ ቅርስ ነው፡፡ በፖርኩ ዝርያቸው ሊጠፉ የተቃረቡና በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የዋልያ፣ ጭላዳ ዝንጀሮና የስሜን ቀይ ቀበሮ ይገኛሉ፡፡ ይህ ውብ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ያለው ፖርክ በያዘው ብዝኃ ሕይወት በዓለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግቧል፡፡



የስሜን ቀይ ቀበሮ



ዋልያ



የጭላዳ ዝንጀሮ

ሥዕል 4.6 የስሜን ተራራ ብሔራዊ ፖርክ ብርቅዬ የዱር እንስሳት

## መ. የጎንደር አብያተ መንግሥታት

የጎንደር አብያተ መንግሥታት በአሥራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን የታነጹና ከፍተኛ የኢትዮድያውያን የኪነ ጥበብ ችሎታ የታየባቸው ቅርሶች ናቸው፡፡

የጎንደር አብያተ መንግሥታት ጥንታዊ የሥነ ሕንጻ ሥልጣኔን የሚያሳዩና የታሪክ ማኅደር በመሆናቸው በዓለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግበዋል፡፡



ሥዕል 4.7 የፋሲል ግንብ ገጽታ በከፊል

የጎንደር አብያተ መንግሥታት በአሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተሠርተው እስካሁን ከነውበታቸው በመቆየታቸው በዓለም ቅርስነት ሊመዘገቡ ችለዋል፡፡


### ሠ. የጥያ ትክል ድንጋዮች

በጥያ ታሪካዊ ሥፍራ ከ36 የሚበልጡ ትክል ድንጋዮች ይገኛሉ፡፡ በትክል ድንጋዮቹ ላይ የተለያዩ ቅርጽና ሥዕሎች ይታያሉ፡፡ የጥያ ትክል ድንጋይ የቀደምት የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤትና የእውቀት መገለጫ በመሆኑ በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል፡፡



ሥዕል 4.8 የጥያ ትክል ድንጋዮች

## ረ. የሐረር ግንብ



ሥዕል 4.9 የሐረር ግንብ

የሐረር ግንብ በአሚር ኑር ኢብን ሙጀሂድ አማካኝነት በ1551 ዓ.ም. (እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር) የከተማውን ሕዝብ ከጥቃት ለመከላከል ተገንብቷል፡፡ ግንቡ አምስት በሮች አሉት፡፡ ይህ ግንብ በመካከለኛው የታሪክ ዘመን በሀገራችን የነበረውን የኪነ ሕንጻ ሥልጣኔ የሚያሳይና ታሪካዊ በመሆኑ በዓለም ቅርስነት ሊመዘገብ ችሏል፡፡

## ሰ.የታችኛው የአዋሽ ወንዝ ሸለቆ

የአዋሽ ወንዝ የታችኛው ሸለቆ በጥንታዊ ቅሪተ አካል የበለፀገ በመሆኑ በዓለም ቅርስነት ሊመዘገብ ችሏል፡፡



ሥዕል 4.10 የታችኛው አዋሽ ወንዝ በከፊል

### ሸ. የታችኛው የኦሞ ወንዝ ሸለቆ

በታችኛው የኦሞ ወንዝ ሸለቆ በተደረገው የከርሠ ምድር ቁፋሮ ጥንታዊ ቅሪተ አካላት ስለተገኙበት በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል፡፡



ሥዕል 4.11 የታችኛው የኦሞ ወንዝ ሸለቆ ገጽታ በከፊል

### ቀ. የኮንሶ መልክዓ ምድር


ኮንሶ በደቡብ ኢትዮጵያ ይገኛል፡፡ በዚህ ቦታ ተራራማ ቦታዎችና እርከኖችን ማስተዋል ይቻላል፡፡ ድሮ በአካባቢው ይኖር የነበረው ሕዝብ አፈሩ በዝናብ እንዳይሸረሸር ለመከላከል እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠበቅ እርከን በመሥራት ይታወቃል፡፡ ይህ የድንጋይ እርከን ለመልክዓ ምድሩ ውበትን አጐናጽፎታል፡፡ ይህም ጥንታዊና ባህላዊ ሥልጣኔን የሚያሳይ በመሆኑ በዓለም ቅርስነት ሊመዘገብ ችሏል፡፡



ሥዕል 4.12 የኮንሶ መልክዓ ምድር

## የቅርስ ጥቅም

ቅርሶች ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነ ውበታዊና ታሪካዊ ጥቅም አላቸው፡፡ ቅርሶች የዘመኑን የሥልጣኔና የእደ ጥበብ እድገት የሚያሳዩ ሕያው ምስክሮች ናቸው፡፡ ቅርሶች የቱሪስት መስህቦች፣ የገቢ ምንጮችና የታሪክ መረጃዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ እንዳይጠፉ፣ እንዳይበላሹና ከሀገር እንዳይወጡ ተገቢ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡






ሥዕል 4.13 ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶቻችን በከፊል

## መልመጃ 4.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. የቅርሶችን አመዳደብ ግለጹ፡፡
2. በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡ የሀገራችንን ቅርሶች ዘርዝሩ፡፡
3. የአዋሽና የኦሞ ሸለቆዎች በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ ያስቻላቸውን ምክንያቶች ግለጹ፡፡
4. የኮንሶ ባህላዊ መልክዓ ምድር በዓለም ቅርስነት የተመዘገበው በምንድን ነው?

## ልማዳዊ ድርጊቶች

ማንኛውም ኅብረተሰብ በጋራ የሚያዳብራቸውና የሚተገበራቸው የአሠራር ሁኔታዎች አሉ፡፡ የአንድ ኅብረተሰብ ልማዳዊ ድርጊቶች በሥራ፣ በሐዘን፣ በደስታ፣ በጋብቻና በሌሎች ተግባራት ይገለጻሉ፡፡ በኅብረተሰብ ውስጥ ጠቃሚና ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አሉ፡፡ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚኖሩ ሕዝቦች የተለያዩ ጠቃሚና ጐጂ ባህላዊ ድርጊቶችን አዳብረዋል፡፡ **ለምሳሌ፡-**

- ልጆችን በሥነ ሥርዓት ኮትኩቶ ማሳደግ
- በመረዳዳት ተከባብሮ መሥራት
- ሥራ ወዳድነት ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶች ናቸው፡፡

በተቃራኒው ደግሞ ለጤና፣ ለማኅበራዊ ግንኙነትና ለእድገት እንቅፋት የሚሆኑ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችም በሕዝብ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ **ለምሳሌም፡-**

- የልጃገረድ ጠለፋ፣
- ግግ መቧጠጥ
- የሴት ልጅ ብልት ግርዛት
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ
- ንቅሳት ወይንም የተለያዩ ቅርጾችን በሰውነት ቆዳ ላይ ማሠራትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

**ተግባር 4.1.2** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያስከትሉትን ተጽእኖ መግለጽ

**መመሪያ-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው፡፡

**የመወያያ ጉዳዮች**

- በአካባቢያችሁ የሚተገበሩ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምን ምን እንደሆኑ ቤተሰቦቻችሁን ወይንም በአካባቢያችሁ የሚገኙ ትላልቅ ሰዎችን በማነጋገር መረጃ አሰባስቡ፡፡
- ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያስከትሉት ጉዳት ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር አቅርቡ፡፡
- ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዴት ልናስወግዳቸው እንደምንችል የመፍትሔ ሐሳቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት በብዙ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ስለዚህ በአካባቢያችን የሚታዩ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ ሁላችንም የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማድረግ አለብን፡፡

## የኢትዮጵያ የቋንቋ ቤተሰቦች

ባህል የአንድ ኅብረተሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረስ የመጣ የአነጋገር፣ የአመጋገብ፣ የአስተሳሰብ፣ የአለባበስና የአኗኗር ሁኔታ ነው። ስለዚህ ቋንቋ የአንድ ሕዝብ የባህል መገለጫ ነው። በኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በአራት የቋንቋ ቤተሰቦች ይመደባሉ። እነርሱም፡-

- የሴም ቋንቋ ምድብ
- የኩሽ ቋንቋ ምድብ
- የኦሟዊ ቋንቋ ምድብ
- የናይሎ ሰሐራዊ ምድብ ናቸው።

በእያንዳንዱ ምድብ የተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

**ለምሳሌ፡-**

ሀ. **በሴም ቋንቋ ምድብ፡-** የአማርኛ፣ የጉራጌኛ፣ የሐረሪ፣ የትግርኛና የዛይ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

ለ. **በኩሽ ቋንቋ ምድብ፡-** የአፋርኛ፣ የአዊኛ፣ የኦሮምኛ፣ የሲዳምኛና የሱማሌኛ ቋንቋዎች ይመደባሉ።

ሐ. **በኦሟዊ ቋንቋ ምድብ፡-** የቡርጂ፣ የባስኬቶ፣ የዶርዜና የወላይትኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

መ. **በናይሎ ሰሐራዊ ቋንቋ ምድብ፡-** የበርታ፣ የአንፌሎ የኑዌርና የአሪ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች በአብዛኛው በሰሜን የሀገራችን ክፍል ይገኛሉ። የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ደግሞ በማዕከላዊና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ይገኛሉ። የኦሟዊ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች በኦሞ ወንዝ ግራና ቀኝ በሚገኙ ቦታዎች ይገኛሉ። የናይሎ ሰሐራዊ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች ደግሞ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የጠረፍ አካባቢዎች ይገኛሉ።

## የሀገራችን ታዋቂ ግለሰቦችና የሕይወት ተሞክሯቸው

ታዋቂ ግለሰብ ለቆመለት ዓላማና ተግባር ጉልህ አስተዋጽኦ በማድረግ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ሰዎች የሚሰጥ መጠሪያ ነው። ሀገራችን የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤትና የትጉህ ሰዎች መፍለቂያ ናት። ሀገራችን ለዘመናት የግዛት ሉአላዊነቷን በልጆቿ አስጠብቃ ኖራለች። በተጨማሪም በተለያዩ የሙያ ዘርፎች በዓለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ፣ በጥረታቸው፣ በስኬታቸውና በአኩሪ ተግባራቸው ለብዙዎች አርአያ የሚሆኑ፣ ውለታቸውና የሕይወት ስኬታቸው ሊነገርላቸው፣ በትውልድ ሊታወቁና ሊታሰቡ የሚገቡ በርካታ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን አሉ። ቀጥለን በተለያዩ የሙያ መስኮች አስተዋጽኦ ያበረከቱ ታዋቂ ግለሰቦች የሕይወት ተሞክሮን እንመልከት።

### በሙዚቃና ሥነ-ጥበብ ታዋቂ ግለሰቦች

በሙዚቃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን አጭር ታሪክ

- **ቅዱስ ያሬድ:-** በሰሜኑ ሀገራችን በስድስተኛው ክፍለ ዘመን በአክሱም ተወለደ:: ቅዱስ ያሬድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበትን የዜማ ድርሰት በማዘጋጀት ይታወቃል:: ቅዱስ ያሬድ ረቂቅ የዜማ ስልቶችን፣ የዜማ ምልክቶችንና ድርሰቶችን በመድረስ የሚታወቅ ኢትዮጵያዊ የዜማ ሊቅ ነበር::

በሥነ ጥበብ አስተዋጽኦ ያደረጉ

- **ሰአሊ አለ ፌለገ ሰላም:-** በ1917 ዓ.ም በሸዋ ተወለዱ:: የሥነ ጥበብ ፍቅር ስለነበራቸው ውጭ ሀገር በመሄድ በከፍተኛ ተቋም ችሎታቸውን አዳብረው ወደ ሀገራቸው በመመለስ በሥዕል ሥራዎቻቸው ታዋቂነትን አትርፈዋል:: የመጀመሪያው የሥዕል ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ በ1950 ዓ.ም. ሲቋቋም የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በመሆን አገልግለዋል:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሚገኘው የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤትም ላደረጉት አስተዋጽኦ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ በስማቸው ተሠይሟል::

### በሥነ ጽሑፍ ታዋቂ ግለሰቦች

ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤልና ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ነበሩ:: ሁለቱም በተባ ብዕራቸው ኢትዮጵያውያን የሥራ ትጋትና ጥልቅ የሀገር ፍቅር ስሜት እንዲላበሱ ያበረታቱና ይመክሩ ነበር:: ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ሀገራቸውን አገልግለዋል:: ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤልም የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ይታወቃሉ:: የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለቱም የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች የክብር ዶክትሬት ሰጥቷቸዋል::



ክቡር ዶክተር ሐዲስ ዓለማየሁ



ክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል

ሥዕል 4.14 ታዋቂ የሥነ ጽሑፍ ሰዎች

## መልመጃ 4.2

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ፡፡**

1. በድሮ ጊዜ ተሠርቶ የተገኘ ማንኛውም ዕቃ ቅርስ ይባላል፡፡
2. አዲስ አበባ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበች ከተማ ናት፡፡
3. በሥራ መረዳዳት ጐጂ ልማዳዊ ድርጊት ነው፡፡
4. ጀግንነት የሚገለጸው በጦር ሜዳ ብቻ ነው፡፡
5. የስሜን ተራራ ብሔራዊ ፖርክ ተፈጥሮአዊ ቅርስ ነው፡፡

**ለ. በ"ሀ" ሥር ያሉትን ቅርሶች በ"ለ"ሥር ከተዘረዘሩት ቦታዎች ጋር አዛምዷቸው፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| ______ 1. ትክል ድንጋይ | ሀ. ላሊበላ |
| ______ 2. ቅሪተ አካል | ለ. ታችኛው የኦሞ ሸለቆ |
| ______ 3. ተፈጥሮአዊ ቅርስ | ሐ. አክሱም |
| ______ 4. የድንጋይ ፍልፍል ሕንጻ | መ. ሐረር |
| ______ 5. የእርከን ሥራ | ሠ. ኮንሶ |
| | ረ. ጎንደር |
| | ሰ. ጥያ |
| | ሸ. የስሜን ተራራ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡት የኢትዮጵያ ቅርሶች________ ናቸው፡፡
   ሀ. ስምንት ለ. ስድስት ሐ. ዘጠኝ መ. አምስት
2. ከኦሟዊ ቋንቋ ምድብ የሚገኘው ቋንቋ የቱ ነው?
   ሀ. ጋፋት ለ. አፋር ሐ. ሲዳማ መ. ቡርጂ
3. ከአብያተ መንግሥታት በቅርስነት የተመዘገበ የትኛው ነው?
   ሀ. ታችኛው የኦሞ ሸለቆ ሐ. ሐረር
   ለ. አክሱም መ. ጎንደር
4. ከሚከተሉት አንዱ በሥነ ጽሑፍ የሚታወቁ እውቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡
   ሀ. ቅዱስ ያሬድ ሐ. ሐዲስ ዓለማየሁ
   ለ. ዶ/ር አክሊሉ መ. አበበ ቢቂላ
5. በስሜን ተራራ ብሔራዊ ፖርክ የማይገኘውን ብርቅዬ እንስሳ ለይታችሁ አውጡ፡፡
   ሀ. የሜዳ አህያ ሐ. ዋልያ
   ለ. ጭላዳ ዝንጀሮ መ. ቀይ ቀበሮ

መ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተስማሚ ቃላት ሙሏቸው፡፡

1. በትግራይ ክልል የሚገኝ በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተዘመገበው ቅርስ_____ ይባላል፡፡
2. የበርታና የኑዌር ቋንቋዎች የ___________ቋንቋ ቤተሰብ ናቸው፡፡
3. ግግን ማስቧጠጥ___________ነው፡፡
4. የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን የሚገኙ በ_______የኢትዮጵያ ክፍል ነው፡፡
5. በዓይን የማይታይና የማይጨበጥ ቅርስ_________ ይባላል፡፡

## 4.2 ማኅበራዊ ግንኙነቶችና እሴቶች

ከንዑስ ርዕሰ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

➢ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በኅብረተሰቡ የሚታወቁ የማኅበራዊ ግንኙነት ዓይነቶችን ትለያላችሁ፡፡
- መተባበርን፣ ለሌሎች ፍቅርና አክብሮት ታሳያላችሁ፡፡
- ቁርጠኝነትና ጤናማ ግንኙነት በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- ማኅበራዊ እሴቶች ለኅብረተሰብ ጠቃሚ መሆናቸውን ትገልጻላችሁ፡፡
- ለማኅበራዊ እሴቶች ምሳሌዎች ትሰጣላችሁ፡፡
- መልካም አስተዳደር ምን እንደሆነ ትገልጻላችሁ፡፡
- የመልካም አስተዳዳር ምንነትን ከዕለታዊ ሕይወታችሁና ከትምህርት ቤታችሁ በመነሣት ምሳሌ ትሰጣላችሁ፡፡

የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

1. በኅብረተሰብ የሚታወቁ ማኅበራዊ ግንኙነቶች
2. ማኅበራዊ እሴቶች
3. መልካም አስተዳደር

**ተግባር 4.2.1** ☛ የቡድን ውይይት

ዓላማ- የማኅበራዊ ግንኙነቶች ዓይነትንና ጠቀሜታን መግለጽ

መመሪያ- ተማሪዎች ከ 4-6 አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡

የመወያያ ጉዳዮች

- ከወላጆቻችሁ ጋር ያላችሁን ግንኙነት ለቡድናችሁ አባላት በመግለጽ በመካከላችሁ ስላለው ልዩነት ተነጋገሩ፡፡
- በትምህርት ቤት ከጓደኞቻችሁና ከመምህራን ጋር ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡
- የቡድኑ አባላት ከጓደኞቻችሁ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ተነጋገሩ፡፡

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማኅበራዊ እንስሳ ነው፡፡ ስለዚህም በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴው ከሌሎች በመግባባትና በመተባበር ይኖራል፡፡ ለማንኛውም ግንኙነት ሥርዓት አለው፡፡ ጤናማ ግንኙነት በሥርዓትና በተረጋጋ መንፈስ ይፈጠራል፡፡ መልካም ግንኙነት ደስተኛና ውጤታማ ያደርጋል፡፡ መልካም ያልሆነ ግንኙነት ተስፋ ያስቆርጣል፤ ለግጭትም ይዳርጋል፡፡ መቻቻል የመልካም ግንኙነት መገለጫ ነው፡፡

## የባልና የሚስት እንዲሁም የልጆች ግንኙነት

ባልና ሚስት የቤተሰብ መሠረት ናቸው፡፡ ወላጆች ቤታቸውን በአግባቡ ለመምራት፣ ልጆችን በሥነ ሥርዓት ማሳደግና ለቁም ነገር ማብቃት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለዚህ በመቻቻልና በመግባባት የመደማመጥና የመወያየት ልምድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡



ሥዕል 4.15 አባት፣ እናት እና ልጆች

የልጆች ስብዕና በቤተሰብና በጓደኛ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ልጆች ገለልተኛ፣ በቀላሉ የሚቆጡና አስቸጋሪ ሆነው ካደጉ ሰብአዊ ግንኙነታቸው ይጐዳል፡፡ ስለዚህም ልጆች የማኅበረሰባቸውን መልካም እሴቶች መላበስ ይገባቸዋል፡፡

**ተግባር 4.2.2** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** ጥሩ ቤተሰባዊ ግንኙነት ለልጆች መልካም ሥነ ምግባር መላበስ ያለውን አስተዋጽኦ መግለጽ

**መመሪያ-** ተማሪዎች ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ተወያዩ፡፡

**የመወያያ ጉዳዮች**

- ሕጻናትን በመልካም ሥነ ምግባር ለማሳደግ ወላጆች ማድረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን ተግባራት ምን ምን እንደሆነ ዘርዝሩ፡፡
- ሕጻናት ከወላጆቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን ተግባራት በመለየት ተወያዩባቸው፡፡

## የመምህርና የተማሪ ግንኙነት

መምህራን የቀለም አባትና እናት ናቸው፡፡ መምህራን ዜጎችን በመልካም ሥነ ምግባር የመቅረጽ ሀገራዊና ሙያዊ ግዴታ አለባቸው፡፡ መምህራን ሕጻናት በእውቀት በልጽገው እንዲያድጉ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡



ሥዕል 4.16 የመምህርና የተማሪዎች መልካም ግንኙነት በክፍል ውስጥ

መምህራን ከተማሪዎቻቸው ፍቅርና ክብር ያገኛሉ፡፡ ተማሪዎችም ሁል ጊዜ ለመምህራቸው አክብሮትና ፍቅር ማሳየት ይገባቸዋል፡፡

**ተግባር 4.2.3** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** የተማሪዎችና የመምህራን መልካም ግንኙነት ያለውን ጠቀሜታ መግለጽ

**መመሪያ-** ተማሪዎች ቡድን በመመሥረት የሚቀጥሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ለመምህራችሁ አክብሮት ማሳየት ለምን ይጠቅማል?
- በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት መኖር አለበት?

## ሌሎች ግንኙነቶች

በአካባቢያችሁ የሚኖሩትን ታላላቆቻችሁንና አረጋውያንን ማክበር እንዲሁም መታዘዝና ፍቅርን ማሳየት አለባችሁ፡፡

**ተግባር 4.2.4** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** የመረዳዳትና የመተባበር ጥቅምን መግለጽ

**መመሪያ-** ተማሪዎች ቡድን በመመሥረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- የመረዳዳትና የመተባበር ጥቅም ምንድን ነው?
- የመረዳዳትና የመተባበር መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

## ማኅበራዊ እሴቶች

ማኅበራዊ እሴት ምንድን ነው? ማኅበራዊ እሴት ለምን ይጠቅማል? ማኅበራዊ እሴት በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ጠቃሚነት ያለውና ለትውልድ የሚተላለፍ አስተሳሰብ ወይንም ተግባር ነው፡፡ የአካባቢያችን ኅብረተሰብ ከለመደው ወግና ባህል ውጭ መሆን ተቀባይነትን ያሳጣል፡፡ ስለዚህ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን በምንኖርበት ኅብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ተግባራትን በመለየት መንቀሳቀስ ይገባናል፡፡ ማኅበራዊ እሴቶች ተቻችሎ ለመኖር፣ ለሰላምና ለእድገት ጠቃሚ ናቸው፡፡

ሰዎች በኃዘንና በደስታ ጊዜ በጋራ የሚያከናውኗቸው ጠቃሚ ማኅበራዊ እሴቶች አሉን፡፡ **ለምሳሌ፡-** እድርና እቁብ፣ አረጋውያንን ማክበርና መደገፍ፣ እንግዳን መቀበል፣ ሥራን በጋራ መሥራት ጠቃሚ ማኅበራዊ እሴቶቻችን ናቸው፡፡

እድር ሰዎች በበጐ ፈቃደኝነት የሚመሠርቱት ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡ በኃዘን ጊዜ ኃዘንተኛውን ማጽናናት፣ የቀብር ሥርዓት ማስፈጸምና እንግዳ ተቀብሎ መሸኘት የእድር አባላት የሚያከናውኑት ተግባር ነው፡፡ የእድር አባላት ለሁሉም በእኩል ደረጃ ያለምንም ልዩነት በኃዘን ጊዜ ተገቢውን ትብብር ያደርጋሉ፡፡ ከመካከላቸው የተቸገረ ሲኖርም ይረዳዳሉ፡፡

እቁብ ደግሞ ሌላው የአካባቢያችን ሰዎች የሚረዳዱበት ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡ ሰዎች ከገቢያቸው ቆጥበው ገንዘብ በማዋጣት በየጊዜው ለአባላቸው በእጣ ወይንም በትብብር መልክ ገንዘብ የሚያበድሩበትና የእቁብ ገንዘብ ለተፈለገው አገልግሎት የሚቆጥቡበት እሴት ነው፡፡



ሥዕል 4.17 የእድር አባላት በስብሰባ ላይ

በአካባቢያችን ኅብረተሰብ አባላት መካከል ግጭት ከተፈጠረ በአካባቢው ያሉ ሽማግሌዎች ግጭቱን በሽምግልና በመፍታት ሰላም እንዲሰፍንና መቻቻል እንዲኖር፣ ሰዎቹ ተቻችለው እንዲኖሩ ያደርጋሉ። ስለዚህም ግጭትን በሽምግልና መፍታት ጠቃሚ ማኅበራዊ እሴታችን ነው።



ሥዕል 4.18 የእቁብ አባላት በስብሰባ ላይ

ኢትዮጵያውያን በእንግዳ ተቀባይነታችንና የተቸገሩ ወገኖችን በመርዳት እንታወቃለን። ብሔራዊ፣ ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን በጋራ በማክበርም እንታወቃለን። በገጠሩ የሀገራችን ክፍል በግብርና የሚተዳደሩ ኢትዮጵያውያን ደግሞ በመረዳዳት ሥራን

የመሥራት ባህል አላቸው። ለምሳሌ:-እርሻን ለማረስ፣ አረም ለማረም፣ አዝመራን ለመሰብሰብ በወንፈል ወይንም በጅጊ ወይንም በደቦ ሥራን በትብብር ይሠራሉ።



ሥዕል 4.19 ሥራን በደቦ መሥራት

**ተግባር 4.2.5** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** የማኅበራዊ እሴቶችን ምንነት መናገር

**መመሪያ-** ተማሪዎች ቡድን በመመሥረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርጉ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- የእድርና የእቁብ ልዩነቶች ምንድን ናቸው?
- በሽምግልና ግጭቶችን መፍታት የሚሰጠው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

## መልካም አስተዳደር

**ተግባር 4.2.6** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** የመልካም አስተዳደርን ጽንሰ ሐሳብና ጥቅም ማስረዳት

**መመሪያ-** ተማሪዎች ከ4 - 6 ባሉ አባላት ቡድን መሥርቱና በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ የጋራ ውይይት አድርጉ።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- መልካም አስተዳደር ምንድን ነው?
- በትምህርት ቤታችሁ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች ምንድን ናቸው?
- የመልካም አስተዳደር መኖር ለምን ይጠቅማል?
- በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ መኖር የሚገባው የመልካም አስተዳዳር መገለጫ ምንድን ነው?

የሕዝብን ሰላምና ጥቅም ለማስጠበቅ፣ እኩልነትና ፍትሕን ለማስፈን የሚደረግ ግልጽነት፣ አሳታፊነት፣ ተጠያቂነትና ዲሞክራሲያዊነት ያለበት አስተዳር የመልካም አስተዳዳር ምሳሌ ነው፡፡ በትምህርት ቤት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ተማሪዎች ተወካዮቻቸውን በግልጽ የሚመርጡበት፣ ለሚታዩ ችግሮች የትምህርት ቤቱ የአመራር አካላት የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ የሚጠይቁበት እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ አስተያታቸውን እንዲሰጡ የሚጠየቁበት አሠራር የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው፡፡

መልካም አስተዳደር የሕዝብን ሰላምና ጥቅም ለማስጠበቅ እኩልነትና ፍትሕን ለማስፈን የሚደረግ ግልጽነት፣ አሳታፊነትንና ተጠያቂነትን ያካትታል:: መልካም አስተዳደር ለሕዝብ እድገትና ለሰላም አስፈላጊ ነው፡፡ መልካም አስተዳደር በትምህርት ቤቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንዲሰፍን ዜጐች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ተማሪዎች መልካም አስተዳደርን በክፍል ውስጥ መለማመድ ትችላላችሁ፡፡ **ለምሳሌ፡-** የክፍላችሁን ተጠሪ በመምረጥ፣ ችግሮቻችሁን በውይይት በመፍታት፣ የጓደኞቻችሁን መብት በማክበር፣ የሚረብሹ ተማሪዎች ካሉ የትምህርት ቤታችሁን ደንብ እንዲያከብሩና የሌሎችን ሰላም መረበሽ እንደማይችሉ በግልጽ በመጠየቅና በመምከር መልካም አስተዳደርን መለማመድ ትችላላችሁ፡፡

## የመልካም አስተዳዳር መገለጫዎች

መልካም አስተዳደር የሕዝብ ሥልጣንና የምጣኔ ሀብት ክፍፍል በተገቢው መልክ የሚታይበት የአስተዳዳር ገጽታ ነው፡፡ የመልካም አስተዳዳር መገለጫዎችን እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

### ሀ. ከፍተኛ ሕዝባዊ ተሳትፎ

ሕዝብ ያለምንም ተጽእኖ መሪዎችን በነጻነት የሚመርጥበትና በጉዳዩ ላይ በቀጥታ የሚወስንበት አሠራር መስፈን የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው፡፡

### ለ. የግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር መስፈን

ማንኛውም ውሳኔ ሕግን ወይንም መመሪያን የተከተለ መሆን አለበት፡፡ ሕዝብ በአካባቢው ስለሚፈጸም ጉዳይና ስለአፈጻጸሙ ሂደት በግልጽ የማወቅና የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ይህን መብት የሚያረጋግጥ አሠራር ማስፈን የመልካም አስተዳደር አንዱ መገለጫ ነው፡፡

### ሐ. የሕግ የበላይነት

መልካም አስተዳደር የዲሞክራሲ (የሕዝብ አስተዳዳር) ዋነኛ መገለጫ ባሕርይ ነው፡፡ ሕግ ለሁሉም ዜጎች እኩል ነው፡፡ ማንም ከሕግ በላይ አይደለም፡፡ ስለዚህም ዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት በእኩል የሚታዩበት፣ ሕግን የሚተላለፉ በሕግ የሚጠየቁበትና መብታቸው

የተጣሰባቸው ዜጎች በሕግ የሚጠይቁበትን አሠራር ማስፈን ሌላው የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው፡፡





ሥዕል 4.20 የመልካም አስተዳደር ውጤቶች፡፡

**ተግባር 4.2.7** ☛ **የቡድን ውይይት**

**ዓላማ-** ማኅበራዊ ተቋማት ለመልካም አስተዳደር መስፈን ያላቸውን ሚና መግለጽ

**መመሪያ-** ተማሪዎች ከ4-6 አባላት ያሉት ቡድን በመመሥረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

- ፖሊስ ለመልካም አስተዳደር መስፈን የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው?
- ፍርድ ቤት ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥ ያለው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

### ፖሊስ

ፖሊስ የተቋቋመው የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት ለመጠበቅ ነው፡፡ ሕዝብ ከቤቱ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲመለስ ሰላም እንዲረጋገጥ የፖሊስ አባላት ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡ ፖሊስ ወንጀለኞችን አድኖ በመያዝና ለፍርድ በማቅረብ የሚያከናውነው ተግባር የመልካም አስተዳዳር መገለጫ ነው፡፡



ሥዕል 4.21 ፖሊስ

### ፍርድ ቤት

ፍርድ ቤት ወንጀለኞች እንደ ጥፋታቸው ቅለትና ክብደት ውሳኔ የሚያገኙበት ተቋም ነው፡፡ የፍርድ ቤቶች ፍትሐዊነት፣ ግልጽ አሠራርና ተጠያቂነት የሚታይበት አሠራር የመልካም አስተዳደር መገለጫ ነው፡፡ ፍርድ ቤት

ዜጎች መብታቸውን የሚያስከብሩበትና የሕግ የበላይነትን የሚያረጋግጡበት መንግሥታዊ ተቋም ነው፡፡




ሥዕል 4.22 ፍርድ ቤት

## መልመጃ 4.3

ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡

1. ተጠያቂነትና ግልጽነት መስፈን ያለበት በትምህርት ቤት ብቻ ነው፡፡
2. ማኅበራዊ እሴቶችን መጣስ ተቀባይነትን ያሳጣል፡፡
3. ጅጊ የመልካም ማኅበራዊ እሴት መገለጫ ነው፡፡
4. መልካም አስተዳደርን በክፍል ውስጥ ማስፈን ያስቸግራል፡፡
5. መልካም አስተዳደር ለሀገር እድገት ጠቃሚ ነው፡፡

ለ. በ"ሀ" ስር የሚገኙትን ማኅበራዊ እሴቶች በ"ለ" ሥር ከቀረቡት መገለጫዎቹ ጋር አዛምዷቸው፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ______1. እድር | ሀ. ሥራን በጋራ የማከናወን ባህል |
| ______2. እቁብ | ለ. ግጭትን ማስወገጃ ባህል |
| ______3. ወንፈል | ሐ. ባህላዊ መረዳጃ ተቋም |
| ______4. ሽምግልና | መ. ባህላዊ ገንዘብ መቆጠቢያ ዘዴ |
| ______5.ፍርድ ቤት | ሠ. ዜጐች መብታቸውን የሚያስከብሩበት ተቋም |
| | ረ. የትምህርት ዕድል የሚያገኙበት ተቋም |
| | ሰ. የጤና አገልግሎት የሚያገኙበት ተቋም |

### ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛን መልስ ምረጡ::

1. የሰዎችን ሐሳብ መቀበልና አለማንቋሸሽ የምን ምልክት ነው?

    ሀ. የትምህርት          ሐ. የመቻቻል

    ለ. የአጉል ባህል          መ. ሌሎችን የማክበር

2. ወንፈል፣ ጅጌና ደቦ በየት አካባቢ የሚዘወተሩ ተግባራት ናቸው?

    ሀ. በገጠር    ለ. በከተማ    ሐ. በትምህርት ቤት    መ. በኳስ ሜዳ

3. ሰላምና ፀጥታን ለማስፈን የሚሠራ ተቋም__________ ነው::

    ሀ. ፖሊስ          ሐ. ፍርድ ቤት

    ለ. ትምህርት ቤት          መ. ባንክ ቤት

4. ጠቃሚ ማኅበራዊ እሴት ያልሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ወላጆችን ማክበር          ሐ. ግጭትን በሽምግልና መፍታት

    ለ. መረዳዳት          መ. ስግብግብነት

5. የመልካም አስተዳደር መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ተጠያቂነት          ሐ. የሕግ የበላይነት

    ለ. ግልጽነት          መ. አድሏዊነት

### መ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. የማኅበራዊ እሴቶች ጥቅም ምንድን ነው?
2. በጥፋተኛ ወይም ወንጀለኛ ግለሰቦች ላይ ውሣኔ የሚሰጥ ተቋም የትኛው ነው?
3. የመልካም አስተዳደር መስፈን ጠቃሜታን ዘርዝሩ::
4. የመልካም ግንኙነት መገለጫዎችን ዘርዝሩ::
5. ማኅበራዊ እሴት ምንድን ነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ኢትዮጵያ ሀገራችን የብዙ ቅርሶች ባለቤት ናት፡፡
- በሀገራችን ከሰማንያ በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡ የሀገራችን ቋንቋዎች በአራት ቤተሰቦች ይመደባሉ፡፡
- በአካባቢያችን ኅብረተሰብ የተለያዩ ጠቃሚና ጎጂ ልማደዊ ድርጊቶች ይከናወናሉ፡፡
- በሀገራችን በሥነጥበብ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በዜማና በሌሎች የሙያ ዘርፎች ለሀገር አኩሪ ተግባራት የፈጸሙ በርካታ ታዋቂ ሰዎች አሉ፡፡
- መልካም አስተዳደር ለእድገትና ለሰላም አስፈላጊ ነው፡፡ መልካም አስተዳደርን በሀገር፣ በአካባቢና በትምህርት ቤት ማስፈን ይቻላል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ቅዱስ ያሬድ በዘመናዊ የሙዚቃ ታሪክ ታዋቂ ግለሰብ ነው።
2. ፓርክ ማለት ቅርሶች የሚሰበሰቡበት ሕንጻ ነው።
3. የኦሞቲክ ቋንቋ በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢ ይነገራል።
4. ሥራን በጋራ መሥራት ጠቃሚ እሴት ነው።
5. መልካም አስተዳደር አስፈላጊ አይደለም።

**ለ. በ "ሀ" ስር ያሉትን ታሪካዊ ሥፍራዎች በ"ለ" ስር ካሉት መገለጫዎች ጋር አዛምዷቸው።**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ኮንሶ | ሀ. በአሥራ ሰባተኛ ክፍለ ዘመን የታነጸ |
| 2. ስሜን ተራራ | ለ. መንፈሳዊ ቅርስ |
| 3. የሐረር ግንብ | ሐ. ትክል ድንጋይ |
| 4. የጎንደር አብያተ መንግሥታት | መ. በአሥራ ስድስተኛ ክፍለ ዘመን የታነጸ |
| 5. ጥያ | ሠ. የእርከን ሥራ |
| | ረ. ተፈጥሯዊ ቅርስ |
| | ሰ. በአሥራ ዘጠነኛ ክፍለ ዘመን የታነጸ |

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. የጎንደር አብያተ መንግሥታት የሚያሳዩት __________ ነው።
   - ሀ. የሥነ ሕንጻ ሥልጣኔን
   - ለ. የሥነ ጽሑፍ ሥልጣኔን
   - ሐ. የሥነ ሥዕል ሥልጣኔን
   - መ. የእርከን ሥራ ሥልጣኔን
2. ከሚከተሉት አንዱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት አይደለም።
   - ሀ. ጠለፋ
   - ለ. የሴት ልጅ ግርዛት
   - ሐ. ደቦ
   - መ. ልመና
3. ሕጻናት ዓይናቸውን ሲታመሙ ምን መደረግ አለበት?
   - ሀ. ማስበጣት
   - ለ. በእጅ ማሸት
   - ሐ. ሐኪም ቤት መውሰድ
   - መ. ቅጠላ ቅጠል ጨምቆ ወደ ዓይን ማስገባት
4. ከሚከተሉት የቋንቋ ቤተሰቦች በሰሜን ኢትዮጵያ በስፋት የሚነገረው የትኛው ነው?
   - ሀ. የሴም
   - ለ. የኩሽ
   - ሐ. ኦሞቲ
   - መ. ናይሎ ሰሃራዊ
5. ከሚከተሉት አንዱ የመንፈሳዊ ዜማ ደራሲ ሊቅ ነው።
   - ሀ. አክሊሉ ለማ
   - ለ. ሐዲስ ዓለማየሁ
   - ሐ. አበበ ቢቂላ
   - መ. ቅዱስ ያሬድ

**መ. በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ትክክለኛውን ቃል ወይም ሐረግ በመሙላት መልሱ፡፡**

1. የታችኛው የኦሞ ወንዝ ተፋሰስ የሚገኘው በ ______________ ኢትዮጵያ ነው፡፡
2. የመጀመሪያው የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ማን ይባላሉ?
3. በዓይን የማናያቸው ረቂቅ ቅርሶቻችን ______________ ይባላሉ፡፡
4. የተጣላን ሰው በሰፈር የሚያስታርቁ ሰዎች __________ ይባላሉ፡፡
5. ወንጀለኛን አድኖ በመያዝ ለፍርድ የሚያቀርብ________ነው፡፡

**ፍተሻ**

*ልታከናውኗቸው የምትችሏቸውን ተግባራት ለመግለጽ ይህን (✓) ምልክት በሣጥኖች ውስጥ በማኖር አመልክቱ፡፡*

1. ዓለምአቀፋዊ እውቅና ያላቸውን የኢትዮጵያን ቅርሶች ስም በመጥቀስ ጠቀሜታቸውን እገልጻለሁ፡፡ ☐
2. የባሕል ምንነትን ለማስረዳት የባሕል ገጽታዎችን እለያለሁ፡፡ ☐
3. የኢትዮጵያ ቋንቋ ቤተሰቦችን ስም በመጥቀስ ለእያንዳንዱ ምሳሌ እሰጣለሁ፡፡ ☐
4. በኢትዮጵያ የሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት የሚያስከትሉትን ጉዳትና የሚገቱበትን ዘዴዎች እገልጻለሁ፡፡ ☐
5. በተለያዩ የሙያ ዘርፎች አስተዋጽኦ ያበረከቱ ኢትዮጵያውያንን ስም በመጥቀስ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እገልጻለሁ፤ እነርሱን በአርአያነት ለመከተል እወስናለሁ፡፡ ☐
6. በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን ግንኙነቶች በመለየት ማኅበራዊ ግንኙነትን ለማዳበርና ለመግባባት የሚረዱ ዕሴቶችን በተግባር እገልጻለሁ፡፡ ☐
7. ከዕለት ሕይወታችሁ በመነሣት መልካም አስተዳዳር ምን እንደሆነ እገልጻለሁ፡፡ ☐